# ዘሐጌ፡ ነቢይ፡

## መቅድም

ሐጌ፡ ማለት፡ መልአከ፡ እግዚ.አብሔር፤ አንድም፡ በዓል፡ ማለት፡ ነው፤

ምንተ፡ ይገብሩ፡ በዕለተ፡ ሐጎሙ፡ እንዲል፣ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ጋድ፡ ነው፤ አባቱ፡ አግታ፣ እናቱ፡ ሲን፡ ይባላሉ፣ ሐጌ፡ ዘካርያስ፡ ሚልክያስ፡ ከሚጠት፡ በኋላ፡ የተነሡ፡ ነቢያት፡ ናቸው፤

እስራኤል፡ በፋርስ፡ በባቢሎን፡ ሳሉ፡ ይህ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ የመጣብን፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ባንሠራ፡ ነው፤ እንግዲህ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ሳንሠራ፡ ሌላ፡ አንሠራም፡ አሉ፣ ከወጡ፡ በኋላ፡ ኢኮነ፡ ጊዜሁ፡ ለሐኒፀ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እያሉ፡ ቤታቸውን፡ የሚሠሩ፡ ሆነዋል፣ ይህን፡ ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አርዕስት፡ ሲሰጡ፡ አርዕስት፡ ሰጥተውታል፣ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ብሎ፡ ያመጣዋል፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለዳርዮስ፡ ንጉሠ፡ ሜደን፣

የሜደን፡ ንጉሥ፡ ዳርዮስ፡ በነገሠ፡ በሁለተኛው፡ ዘመን፡ የዘሩባቤል፡ አልጸናምና፡ በዳርዮስ፡ ቆጠረ፤

በሳድስ፡ ወርኅ፣

ባስድስተኛ፡ ወር፡ በመስከረም፤

አመ፡ ርእሰ፡ ሠርቅ፣

የመስከረም፡ መባቻ፤

ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ በእደ፡ ሐጌ፡ ነቢይ፣

በሐጌ፡ ቃል፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ መጣ፡ ተነገረ፤

ወይቤሎ፡ በሎ፡ ለዘሩባቤል፡ ወልደ፡ ሰላትያል፡ ዘሕዝበ፡ ይሁዳ፣

ከይሁዳ፡ ወገን፡ የተወለደ፡ የሰላትያል፡ ልጅ፡ ዘሩባቤልን፡ እንዲህ፡ በለው፤

ወለዮሴዕ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፣

የዮሴዴቅ፡ ልጅ፡ ደጉን፡ ካህን፡ ዮሴዕን፡ እንዲህ፡ በለው፤



፪፤ ወበሉሙ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ በላቸው፤

ዝንቱ፡ ሕዝብ፡ ይቤሉ፡ ኢኮነ፡ ጊዜሁ፡ ለሐኒፀ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፣

ሕዝቡ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ለመሥራት፡ ጊዜው፡ አይደለም፡ ይላሉ፡ በላቸው፤ ሐተታ፡ እስራኤል፡ በባቢሎን፡ ሳሉ፡ ከባቢሎን፡ ብታወጣን፡ ቤተ መቅደስን፡ ሳንሠራ፡ ቤታችንን፡ አንሠራም፡ ብለው፡ ተሳሉ፣ እግዚአብሔር፡ በቸርነቱ፡ ከባቢሎን፡ አወጣቸው፣ እነዚያ ግን፡ ከወጡ፡ በኋላ፡ ቤታቸውን፡ እየሠሩ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ለመሥራት፡ ጊዜው፡ አይደለም፡ እያሉ፡ ዝም፡ ብለው፡ ተቀምጠዋል፣ ዳዊት፡ እመ፡ እግዚአብሔር፡ ኢሐነፀ፡ ቤተ፡ ከንቶ፡ ይፃምዉ፡ እለ፡ የሐንፁ፡ ብሎ፡ ዘልፏቸዋል፣ ኢሳይያስም፡ ሰማይኒ፡ መንበርየ፡ ብሎ፡ ዘልፏቸዋል፣ ከዚህም፡ እንዲህ፡ አለ፤

፫፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ በእደ፡ ሐጌ፡ ነቢይ፣

በሐጌ፡ ቃል፡ የእግዚአብሔር፡ ተነገረ፤

፬፤ ወይቤሎሙ፡ እምጊዜሁ፡ ለክሙ፡ ከመ፡ አንትሙ፡ ትንበሩ፡ ውስተ፡ ቤት፡ ጥፉር፣

ከባቢሎን፡ ከወጣችሁ፡ ጀምሮ፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ለመሥራት፡ አልሆነላችሁም፣ እናንተ፡ በተጋረደ፣ በተነጠፈ፡ ቤት፡ ተቀምጣችኋል፡

ወቤትየሰ፡ ምዝቡር፣

ቤቱ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ግን፡ ፈርሷል፤ አንድም፡ እንዘ፡ ቤትየ፡ ምዝቡር፣ ቤተ፡ መቅደስ፡ ፈርሶ፡ ሳለ፡ እናንተ፡ በተጋረደ፡ በተነጠፈ፡ ቤት፡ ተቀምጣችኋል፤

፭፤ ወይእዜኒ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፣

አሁንም፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ሐልዩዎ፡ እስኩ፡ በልብክሙ፡ ለኵሉ፡ ፍናዊክሙ፣

በልቡናችሁ፡ አነዋወራችሁን፡ እስቲ፡ አስቡት፤

፮፤ እመ፡ ዘራእክሙ፡ ብዙኀ፡ ወአዕተውክሙ፡ ኅዳጠ፣

ብዙ፡ ዘርታችሁ፡ ጥቂት፡ ታገባላችሁ፤

ትበልዑ፡ ወኢትፀግቡ፣

ትበላላችሁ፡ አትጠግቡም፤

ትሰትዩ፡ ወኢትረውዩ፣

ትጠጣላችሁ፡ አትረኩም፤

www.ethiopianorthodox.org

ትትከደኑ፡ ወኢትመውቁ፤

ትለብሳላችሁ፡ አይሞቃችሁም፤

ወዘሂ፡ ያስተጋብዕ፡ አስቦ፡ አስተጋብአ፡ ውስተ፡ ዕቁር፡ ስቁር፤

ደመወዙን፡ የተቀበለ፡ ሰው፡ ለዚህ፡ ሌላ፡ ዕቃ፡ እፈልግለ ታለሁ፡ ብሎ፡ በሰባራ፡ ማድጋ፡ በቀዳዳ፡ ሸልቻ፡ ያኖረዋል፤

፯፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ ሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ሐልዩ፡ ፍናዊክሙ፤

አነዋወራችሁን፡ አስቡ፤

፰፤ ዕርጉ፡ ደብረ፡ ወግዝሙ፡ ዕፀወ፤

ከተራራ፡ ላይ፡ ወጥታችሁ፡ እን ጨቱን፡ ቁረጡ፤

ወሕንፁ፡ ቤተ፤

ቤተ፡ መቅደስን፡ ሥሩ፤

ወአሠምሮ፡ ወእሴብሖ፡ ይቤ፡ እግዚ አብሔር፤

ቤተ፡ መቅደስን፡ አከናውነዋ ለሁ፤ አከብረዋለሁ፡ አለ፡ እግዚ አብሔር፤

፱፤ ርኢክሙ፡ ብዙኀ፡ ወአኅ፡ ኅዳጠ፤

አዝመራውን፡ በርሻው፡ ጥቂት፡ ያይደለ፡ ብዙ፡ ሆኖ፡ አያችሁት፤

ወአባዕክሙ፡ ቤተክሙ፡ ወነፋሕክዎ፤

ወደቤት፡ ባገባችሁ፡ ጊዜ፡ በረ ከት፡ አሳጣሁት፤

በእንተ፡ ዝንቱ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚ አብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ሁሉን፡ የሚ ገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

እስመ፡ ቤትየ፡ ምዝቡር፤

ቤቴ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ፈርሷልና፤ አንድም፡ እንዘ፡ ቤትየ፡ ምዝ ቡር፡ ቤቴ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ፈርሶ፡ ሳለ፤

ወአንትሙሰ፡ ታጸንዑ፡ አብያቲክሙ፡ ኵልክሙ፤

እናንተ፡ ሁላችሁም፡ ቤታች ሁን፡ ታጸናላችሁ፤

፲፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ያቀውም፡ ሰማይ፡ ዝናመ፡ እምላዕሉ፤

ስለዚህ፡ ነገር፡ ከምድር፡ በላይ፡ ያለ፡ ሰማይ፡ ዝናም፡ ለዘር፡ ጠል፡ ለመከር፡ ይነሣል፤

ወምድርኒ፡ ኢትሁብ፡ ፍሬሃ፤

ምድርም፡ የዘሩባትን፡ አታበ ቅልም፤ የተከሉባትን፡ አታ ጸድቅም፤

፲፩፤ ወአመጽእ፡ ኵናተ፡ ላዕለ፡ በሐውርት፤

በሀገሩ፡ ሁሉ፡ ድርቅ፡ ረኃብ፡ አመጣለሁ፤

ወላዕለ፡ እክል፡ ወወይን፡ ወቅብዕ፤

በእህሉ፤ በወይኑ፤ በዘይቱ፡ ላይ፡ ድ[illegible]



ወላዕለ፡ ኵሉ፡ ዘትፈሪ፡ ምድር፤

ምድርም፡ በምታስገኘው፡ ሁሉ፡ ድርቅ፡ አመጣለሁ፤

ወላዕለ፡ ሰብእ፡ ወእንስሳ፤

በሰውም፡ በእንስሳውም፡ ላይ፡ ድርቅ፡ አመጣለሁ፤

ወላዕለ፡ ኵሉ፡ ተግባረ፡ እደዊክሙ፤

በጃችሁ፡ ሥራ፡ ላይ፡ ሁሉ፡ ድርቅ፡ አመጣለሁ፤

፲፪፤ ወሰምአ፡ ዘሩባቤል፡ ወልደ፡ ሰላትያል፡ ዘሕዝበ፡ ይሁዳ፤

ከነገደ፡ ይሁዳ፡ የተወለደ፡ የሰ ላትያል፡ ልጅ፡ ዘሩባቤል፡ ሰማ፤

ወዮሴዕ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፡

ደጉ፡ ካህን፡ የዮሴዴቅ፡ ልጅ፡ ዮሴዕ፡ ሰማ፤

ወኵሎሙ፡ ሕዝብ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ሰምዑ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፤

ከሞት፡ የቀሩት፡ ወገኖች፡ ሁሉ፡ የፈጣሪያቸውን፡ የእግዚአብሔ ርን፡ ነገር፡ ሰሙ፤

ወቃለ፡ ሐጌ፡ ነቢይ፡ ዘከመ፡ ለአኮ፡ እግ ዚአብሔር፡ አምላኮሙ፡ ኀቤሆሙ፤

ፈጣሪያቸው፡ እግዚአብሔር፡ ወደሳቸው፡ የላከው፡ የነቢዩን፡ የሐጌን፡ ቃል፡ ሰሙ፤

ወፈርሁ፡ ሕዝብ፡ እምቅድመ፡ ገጹ፡ ለእግዚአብሔር፤

ከእግዚአብሔር፡ ከገጸ፡ መዓቱ፡ [illegible]፡ ፈሩ፤

፲፫፤ ወይቤሎሙ፡ ሐጌ፡ መልአኮ፡ ለእግዚአብሔር፡ ለሕዝብ፡ አነ፡ ምስሌ ክሙ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር፡ አገልጋይ፡ የሚ ሆን፡ ሐጌ፡ ሕዝቡን፡ ከናንተ፡ ጋራ፡ በረድኤት፡ አለሁ፡ አለ፡ እግዚአብሔር፡ አላቸው፤

፲፬፤ ወአንሥአ፡ እግዚአብሔር፡ መንፈሰ፡ ዘሩባቤል፡ ወልደ፡ ሰላትያል፡ ዘሕዝበ፡ ይሁዳ፤

ከነገደ፡ ይሁዳ፡ የተወለደ፡ የሰ ላትያልን፡ ልጅ፡ የዘሩባቤልን፡ ልቡናውን፡ እግዚአብሔር፡ አነሣሣ፤

ወመንፈሰ፡ ዮሴዕ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፤

የዮሴዴቅን፡ ልጅ፡ የደጉን፡ ካህን፡ የዮሴዕን፡ ልቡና፡ አነሣሣ፤

ወመንፈሰ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ሕዝብ፤

አባቶች፡ አልቀው፡ የቀሩ፡ የል ጆችን፡ ልቡናቸውን፡ አነሣሣ፤

ወቦኡ፡ ይግበሩ፡ ግብረ፡ ቤተ፡ እግዚ አብሔር፡ አምላኮሙ፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ የእግዚአብ ሔርን፡ ማደሪያ፡ ቤተ፡ መቅደ ስን፡ ይሠሩ፡ ዘንድ፡ ወደፊ ሰው፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ገቡ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፪

፩፤ አመ፡ ፳ወ፬ ለሳድስ፡ ወርኀ፣

በስድስተኛው፡ ወር፡ በመስከ ረም፡ በሃያ፡ አራት፡ ቀን፤

በካልዕ፡ ዓመት፣

ዳርዮስ፡ በነገሠ፡ በሁለተኛው፡ ዓመት፤

፪፤ ወበሳብዕ፡ ወርኀ፣

በሰባተኛው፡ ወር፡ በጥቅምት፤

በሰዱሱ፡ ለጽልመት፣

ጨረቃ፡ ብርሃኗን፡ በአጣች፡ ሕፀፅ፡ ባደረገች፤ አንድም፡ ሠርቅ፡ ባደረገች፣ ጨለማዋን፡ በአጣች፡ በስድስተኛው፡ ቀን፤

ነበበ፡ እግዚአብሔር፡ በአፈ፡ ሐጌ፡ ነቢይ፣

እግዚአብሐሔር፡ በነቢዩ፡ በሐጌ፡ ቃል፡ ተናገረ፤

፫፤ ወይቤሎ፡ በሎ፡ ለዘሩባቤል፡ ወልደ፡ ሰላትያል፡ ዘሕዝበ፡ ይሁዳ፣

የሰላትያል፡ ልጅ፡ ዘሩባቤልን፡ እንዲህ፡ በለው፡ አለው፤

ወለዮሴዕ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፣

የዮሴዴቅን፡ ልጅ፡ ደጉን፡ ካህን፡ ዮሴዕን፡ እንዲህ፡ በለው፤

ወለኵሎሙ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ሕዝብየ፣

አባቶች፡ አልቀው፡ የቀሩ፡ ወገ ኖቼን፡ ሁሉ፡ እንዲህ፡ በላቸው፤

፬፤ ወይቤ፡ መኑ፡ እምኔክሙ፡ ዘር እዮ፡ ለዝንቱ፡ ቤት፡ ትርሲቶ፡ ዘትካት፣

ከናንተ፡ ወገን፡ የቤተ፡ መቅደ ስን፡ የቀደመውን፡ ጌጥ፡ ያየ፡ ማነው፤

ወእፎ፡ ትሬእይዎ፡ ይእዜ፡ አንትሙ፡ ከመ፡ ዘኢሀሎ፡ ቅድሜክሙ፣

ፈርሶ፡ ሳለ፡ እንዳልፈረሰ፡ የም ታዩት፡ አይደለም፤ አንድም፡ ፈርሶ፡ ሳለ፡ እንዳልፈረሰ፡ ለምን፡ ታዩታላችሁ? እንዳል ነበረ፡ ሆኖ፡ የለም?

፭፤ ወይእዜኒ፡ ጽናዕ፡ ዘሩባቤል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፣

እግዚአብሔር፡ ዘሩባቤልን፡ ጽና፡ አለው፤

ወይጽናዕ፡ ዮሴዕ፡ ወልደ፡ ዮሴዴቅ፡ ካህን፡ ዓቢይ፣

የዮሴዴቅ፡ ልጅ፡ ደጉ፡ ካህን፡ ዮሴዕም፡ ይጽና፤

ወይጽንኡ፡ አሕዛበ፡ ምድር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፣

ሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ይጽኑ፡ አለ፡ እግ ዚአብሔር፤



ወይግበሩ፣

ቤተ፡ መቅደስን፡ ይሥሩ፤

ወእነ፡ ምስሌክሙ፡ ሀሎኩ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በረድኤት፡ ከናንተ፡ ጋር፡ እኖ ራለሁ፡ አለ፤

፮፤ ወመንፈስየ፡ ይቀውም፡ ማዕ ከሌክሙ፤

መልአኩ፡ በመካከላችሁ፡ ይቆ ማል፤ አንድም፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ ያድርባችኋል፤

፯፤ ተአመኑ፣

እመኑ፤

ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ ሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ዓዲ፡ ምዕረ፡ አነ፡ አድለቀልቃ፡ ለሰ ማይ፡ ወለምድር፣

ዳግመኛ፡ ሰማይንና፡ ምድርን፡ በሚጠት፡ አነዋውጣታለሁ፤ ዓዲ፡ ማለቱ፡ ለደብረ፡ ሲና፡ ነው፤ አንድም፡ በዕለተ፡ ስቅለት፡ አና ውጣታለሁ፣ ዓዲ፡ ማለቱ፡ ለዕ ለተ፡ ምጽአት፡ ነው፤ አን ድም፡ በዕለተ፡ ምጽአት፡ አናው ጣታለሁ፣ ዓዲ፡ ማለቱ፤ ለዕ ለተ፡ ስቅለት፡ ነው፤ ልዑላ [illegible]ለሁ፤

ለባሕር፡ ወለየብስ፣

ከተማውን፡ ገጠሩን፡ አነዋ ውጣለሁ፤

፰፤ ወአድለቀልቆሙ፡ ለኵሎሙ፡ አሕዛብ፣

ሕዝቡን፡ ሁሉ፡ አነዋውጣቸ ዋለሁ፤

ወአመጽእሙ፡ ለከ፡ ድኅሬሆሙ፡ ለኵ ሎሙ፡ አሕዛብ፣

ኅግ፡ ማኅግ፡ እስራኤልን፡ ተከ ትለው፡ እንዲወጡ፡ አደርጋ ቸዋለሁ፤

ወእመልዖ፡ ለዝንቱ፡ ቤት፡ ትርሲቶ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ የቀደመውን፡ ጌጥ፡ እመላዋለሁ፡ አለ፤ ኅግ፡ ማኅግ፡ ተቀራደው፡ አልቀው፡ በነሱ፡ ወርቅ፡ ዘሩባቤል፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ሠርቷልና፤

፱፤ ዚአየ፡ ውእቱ፡ ወርቅ፡ ወብ ሩር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብ ሔር፡ ወርቅና፡ ብር፡ የኔ፡ ገንዘብ፡ ነው፡ አለ፤ ወለዘፈ.ቀ ድኩ፡ እሁቦ፡ ብለው፡ መና ቀርያን፡ ወርቅ፡ ጨምረውበታል፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ ወይኄይስ፡ ትርሲቱ፡ ለዝንቱ፡ ቤት፡ ደኃሪ፡ እምቀዳሚ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤ ቤተ፡ መቅደስ፡ ከመሠራቱ፡ አለመሠራቱ፡ ይሻላል፤ ይህስ፡ ድንቅ፡ አይደለም፡ ብሎ፡ ሰሎሞን፡ ከሠራው፡ ዘሩባቤል፡ የሠራው፡ ይበልጣል፤ ይኸም፡ አይደለ፤ በዘሩባቤል፡ ጊዜ፡ በአንድ፡ እጃቸው፡ ጦር፤ በአንድ፡ እጃቸው፡ ጠጠር፡ ይዘው፡ ሠርተውታል፡ ብሎ፡ ከዘሩባቤል፡ የሄሮድስ፡ ወልደ፡ ሐንዶፌር፡ ይበልጣል፤ አንድም፡ ከቤተ፡ መቅደስ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ይበልጣል፤

ወእሁብ፡ ሰላመ፡ ለዝንቱ፡ ብሔር፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤ በኢየሩሳሌም፡ ፍቅር፡ አንድነትን፡ እሰጣለሁ፡ አለ፤

ወሰላመ፡ ለኵሉ፡ ነፍስ፡ እንተ፡ ትትጌበር፤

ቤተ፡ መቅደስን፡ ለምትሠራ፡ ነፍስ፡ ሁሉ፡ ፍቅር፡ አንድነትን፡ እሰጣለሁ፡ አለ፤

ወይትነሣእ፡ ዝንቱ፡ ሕዝብ፤

ይህ፡ ወገን፡ ቤተ፡ መቅደስን፡ ለመሥራት፡ ይነሣ፤

፲፤ አመ፡ ፳ ወ ፬ ለታስዕ፡ ወርኅ፤

በዘጠነኛ፡ ወር፡ በታኅሣሥ፡ በሃያ፡ አራት፡ ቀን፤

በካልዕ፡ ዓመተ፡ መንግሥቱ፡ ለዳርዮስ፤

ዳርዮስ፡ በነገሠ፡ በሁለተኛ፡ ዘመን፤

ኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ሐጌ፡ ነቢይ፤

ከነቢዩ፡ ከሐጌ፡ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ መጣ፡ ተነገረ፤

፲፩፤ ወይቤሎ፡ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፡ በለው፤

ተሣአሎሙ፡ ለካህናቲከ፡ ሕገ፤

ካህናቱን፡ ብያኔ፡ ጠይቃቸው፤

ወበሎሙ፤

እንዲህ፡ በላቸው፤

፲፪፤ እመ፡ ለከፎ፡ ለሰብእ፡ ሥጋ፡ ቅዱስ፡ ጽንፈ፡ ልብሱ፤

በልብሱ፡ ጫፍ፡ ክቡሩን፡ መሥዋዕት፡ ቢነካው፤ ንጹሑ፡ ሰው፡ ቅዱሱን፡ መሥዋዕት፡ ቢነካው፤

ወለከፎ፡ በዘፈረ፡ ልብሱ፤

በልብሱ፡ ጫፍ፡ ቢነካው፤

እመሂ፡ ኅብስተ፡ ወእመሂ፡ ወይን፤

ኅብስትም፡ ቢሆን፡ ወይንም፡ ቢሆን፤

እመሂ፡ ብሱል፡ ዘኮነ፡ እምእክል፤

ከእህል፡ ወገን፡ የበሰለም፡ ቢሆን፡ ማለት፡ ገንፎ፡ መንካከ፡ ቢሆን፤



ወእመሂ፡ እምቅብዕ፡ ቅዱስ፤

ከከበረ፡ ከዘይት፡ ወገንም፡ ቢሆን፤

ኢይትቄደስኑ፤

ይነጻል፡ አይነጻም፡ አላቸው፤

ወይቤሉ፡ ካህናት፡ ይትቄደስ፤

የእስራኤል፡ ሕግ፡ አሕዛብን፡ ያከብራል፡ አሉ፡ ማለት፡ አሕዛብ፡ ከእስራኤል፡ ቢጋቡ፡ ይከብራሉ፤

፲፫፤ ወይቤሎሙ፡ መልአክ፡ እመ ሰኬ፡ ለከፎ፡ ርኩስ፡ ወስዑበ፡ ነፍስ፡ ኢይረኩስኑ፡ እምዝንቱ፤

ከዚህ፡ ሁሉ፡ ወገን፡ ዝኤት፡ ያገኘው፡ ርኵስነት፡ ያለው፡ ሁሉ፡ ቢነካው፡ አይረክስምን፤ እምዝንቱ፤ ከዚህ፡ ሁሉ፡ የተነሣ፡ አይረክስምን፡ አላቸው፤

ወይቤሉ፡ ካህናት፡ ይረኵስ፤

የአሕዛብ፡ ሕግ፡ እስራኤልን፡ ያረክሳቸዋል፡ አሉ፤ ማለት እስራኤል፡ ከአሕዛብ፡ ቢጋቡ፡ ይረክሳሉ፤

፲፬፤ ወይቤሎሙ፡ ሐጌ፡ መልአክ፡ ከማሁኬ፡ ዝንቱ፡ ሕዝብ፡ ወነገድ፡ በቅድሜየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ሐጌ፡ እንዲህ፡ አላቸው፤ ይህ፡ ነገድ፤ ይህ፡ ወገን፡ በፊቴ፡ አሁን፡ እንደተናገርሁት፡ ነው፡ ... እግዚአብሔር፤

ወከማሁኬ፡ ኵሉ፡ ተግባረ፡ እደዊሆሙ፡ ወኵሉ፡ ዘቀረበሙ፡ ይረኵስ፤

አሁን፡ እንደተናገርሁት፡ የእጃቸው፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ወደሳቸው፡ የቀረበው፡ ሁሉ፡ ከአሕዛብ፡ ቢጋቡ፡ ይረክሳሉ፤ እሳቸው፡ ግን፡ ቢጋቡ፡ አይረክሱም፤

በእንተ፡ ዘተረፎሙ፤

ከልጆቻቸው፡ ጋራ፡ ስለተጋቡ፡ ይረክሳሉ፤

ወበጽባሕ፡ ይሳቀዩ፡ በቅድመ፡ ሕማሞሙ፤

ከአሕዛብ፡ አስቀድመው፡ መከራ፡ ይቀበላሉ፤ አንድም፡ ከፅርዕ፡ መከራ፡ በፊት፡ መከራ፡ ይቀበላሉ፤

ወይጸልዕዎሙ፡ ለእለ፡ ይጌሥጽዎሙ፡ በአናቅጽ፤

በአደባባይ፡ የሚመክሯቸውን፤ የሚያስተምሯቸውን፡ ነቢያት፡ ካህናትን፡ ይጠሏቸዋል፤

፲፭፤ ወይእዜኒ፡ ሐልዩ፡ በልብክሙ፡ ዘእምቅድመ፡ ቀዳሚት፡ ዕለት፡ ወዘእምቅድሜሃ፤

ቤተ፡ መቅደስ፡ ከመሠራቷ፡ አስቀድሞ፡ ከተሠራችም፡ በኋላ፡ የሆነውን፡ አስቡ፤ አንድም፡ ከተሠራች፡ ወዲህ፡ ከመሠራቷም፡ አስቀድሞ፡ የሆነውን፡ አስቡ፤

www.ethiopianorthodox.org

ወዘእንበለ፡ ያንብሩ፡ ዕብነ፡ ዲበ፡ ዕብን፡ ውስተ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፤

ቤተ፡ መቅደስን፡ ለመሥራት፡ ደንጊያን፡ በደንጊያ፡ ላይ፡ ሳያኖሩ፡ የሆነውን፡ አስቡ፤

መኑ፡ አንትሙ፤

እስ፡ መኑ፡ ሲል ነው፤ እናንት፡ እነማናችሁ፤

፲፯፤ እመ፡ ትዘርዑ፡ እሥራ፡ ሰገመ፡ ወታእትዉ፡ ዐሥረ፡ ሰገመ፤

ሃያ፡ ማድጋ፡ ገብስ፡ ትዘራላችሁ፡ ዐሥር፡ ማድጋ፡ ታገባላችሁ፤

ወትበውዑ፡ ውስተ፡ ምክያድ፡ ትትቀድሑ፡ ሃምሳ፡ ጸህበ፡ ወትቀድሑ፡ ዕሥራ፤

አምሳ፡ ፊቀን፡ ትቀዱ፡ ዘንድ፡ ወደወይኑ፡ አውድማ፡ ትገባላችሁ፡ ሀያ፡ ፊቀን፡ ትቀዳላችሁ፤

፲፰፤ ቀሠፍኩክሙ፡ በዓባር፡ ወበበረድ፤

በበረድ፡ በድርቅ፡ አጠፋኋችሁ፤

ወበኵሉ፡ ተግባረ፡ እደዊክሙ፤

በእጃችሁ፡ በምትሠሩት፡ ሥራ፡ ሁሉ፡ ድርቅ፡ አመጣሁባችሁ፤

ወኢነሳሕክሙ፡ ወኢተመየጥክሙ፡ ኀቤየ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ወደኔ፡ አልተመለሳችሁም፡ አለ፤

፲፱፤ ሐልዩ፡ በልብክሙ፡ ዘእምቅድመ፡ ቀዳሚት፡ ዕለት፤

ሥራ፡ ከጀመራችሁበት፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ ያለ፡ መጠቀማችሁን፡ አስቡ፤

ወዘእምድኅሬሃ፤

ከዚያም፡ በኋላ፡ ያለውን፤ ዘድኅሬየ፡ እመልዕ፡ እንዲል፤ አንድም፡ ከሰባ፡ ዘመን፡ ከመጀመሪያው፡ ጀምሮ፡ የሆነውን፡ አስቡ፤ እንግዲህም፡ ወዲህ፡ የሚሆነውን፡ አስቡ፤

ዘእምአመ፡ ዕሥራ፡ ወረቡዑ፡ ለታስዕ፡ ወርኅ፤

ከዘጠነኛ፡ ወር፡ ከታኅሣሥ፡ ሃያ፡ አራት፡ ቀን፡ ጀምራችሁ፤

ዘእምአመ፡ ሣረሩ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ተዘከርዎ፡ በልብክሙ፤

ቤተ፡ እግዚአብሔርን፡ ከሠራችሁበት፡ ቀን፡ ጀምሮ፡ የሆነውን፡ በልቡናችሁ፡ አስቡ፤

፳፤ ወትሬእዩ፡ በውስተ፡ ምክያድ፡ እክለ፡ ወወይነ፤

እህሉን፤ ወይኑን፡ በአውድማ፡ ትርፍርፍ፡ ብሎ፡ ታዩታላችሁ፤

ወበለስ፡ ወሮማነ፡ ወዘይተ፡ ወኵሎ፡ ዕፀ፡ ዘይፈሪ፡ እባርክ፡ እምዮም፤

በለሱን፤ ሮማኑን፤ ዘይቱን፡ የሚያፈራውን፡ እንጨት፡ ሁሉ፡ ከዛሬ፡ ጀ[illegible]



፳፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ በዳግም፡ ኀበ፡ ሐጌ፡ ነቢይ፤

ዳግመኛ፡ ከሐጌ፡ ዘንድ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ መጣ፡ ተነገረ፤

አመ፡ ዕሥራ፡ ወረቡዑ፡ ለታስዕ፡ ወርኅ፤

በዘጠነኛ፡ ወር፡ በታኅሣሥ፡ ሀያ፡ አራት፡ ቀን፡ ከሐጌ፡ ዘንድ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ መጣ፡ ተነገረ፤

ወይቤሎ፡ እግዚአብሔር፡ ለመልአክ፤

እግዚአብሔር፡ ሐጌን፡ እንዲህ፡ አለው፤

፳፪፤ በሎ፡ ለዘሩባቤል፡ ወልደ፡ ሰላትያል፡ ዘሕገበ፡ ይሁዳ፤

ከይሁዳ፡ ወገን፡ የተወለደ፡ የሰላትያል፡ ልጅ፡ ዘሩባቤልን፡ እንዲህ፡ በለው፤

ናሁ፡ አድለቀልቃ፡ ለሰማይ፡ ወለምድር፤

በጎግ፡ በማጎግ፡ ጊዜ፤ አንድም፡ በሐሳዊ፡ መሲሕ፡ ጊዜ፡ ልዑላኑን፡ ትሑታኑን፡ አነዋውጣቸዋለሁ፤

ወለባሕር፡ ወለየብስ፤

ከተማውን፡ ገጠሩን፡ አጠፋዋለሁ፤

፳፫፤ ወእገፈትዕ፡ መናብርቲሆሙ፡ ለነገሥት፤

የነገሥታቱን፡ ዙፋን፡ አጠፋዋለሁ፤

ወእገፈትዕ፡ ሠረገላ፡ ወመስተዕዕናነ፤

ሠረገላውን፡ በሠረገላ፡ የተቀ[illegible]

ወይወርዱ፡ መስተዕዕናን፡ ምስለ፡ አስይፍቲሆሙ፡ ኀበ፡ ቢጾሙ፤

ፈረሰኞች፡ በሠረገላቸው፡ እያሆኑ፡ ሰይፋቸውን፡ ይዘው፡ ወደሚጠፉበት፡ ቦታ፡ ይሄዳሉ፤ ከባልንጀሮቻቸው፡ ጋራ፡ ይቀራደዳሉ፤

፳፬፤ ይእተ፡ አሚረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

ወእነሥአከ፡ ዘሩባቤል፡ ወልደ፡ ሰላትያል፤

የሰላትያል፡ ልጅ፡ ዘሩባቤል፡ በኢየሩሳሌም፡ አነግሥሃለሁ፤

ወእሬስየከ፡ ከመ፡ ማዕተብ፤

በቀኝ፡ እጅ፡ እንዳለ፡ ኀቲም፡ ቀለበት፡ አደርግሃለሁ፤ አንድም፡ እንደ፡ ዳዊት፡ አደርግሃለሁ፤

እስመ፡ ኪያከ፡ ኃረይኩ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ አንተን፡ መርጫለሁ፡ ብሏልና፤

ተፈጸመ፡ ዘሐጌ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ የሃሉ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፤

ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤ አነሣሥቶ፡ ለአስጀመረን፤ አስጀምሮ፡ ለአስፈጸመን፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፤ አሜን።

www.ethiopianorthodox.org